## በጦር ሃይል ሰላማዊ ሰልፍን ማፈን የወያኔ መንግስት ያለፉት 22 ዓመታት ድርጊት ቀጣይ ኣካል ነው

*<u>ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር የተሰጠ መግለጫ</u>*

በኢትዮጵያ ተከታታይ ኣምባገነን ስርዓቶች በተለያየ መልኩ የሚፈፅሙት ጭቆናና ዝርፍያ በኢትዮጵያ ተጨቋኝ ህዝቦች በተለይም በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያደረሰው ጉዳት በትዕግስት ከማይታለፍበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የኦሮሞ ህዝብ የሰብዓዊ መብቶችንና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን በማንሳት ለረዥም ዓመታት ታግሏል። ይኸው የኦሮሞ ህዝብ በገዢ ስርዓቶች ላይ ያካሄደውና እያካሄደ ያለው ትግል፡ ዛሬ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በመሸጋገር በመላው ኦሮሚያ ውስጥ ወደ ህዝባዊ ዓመፅ ተቀይሯል። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መንግስታት የኦሮሞ ህዝብ በሰላማዊ መንገድ ያቀረበውን ጥያቄ ኣድምጠው መፍትሄ ከማበጀት፡ ሃይልን መጠቀም የሚመርጡ መሆናቸው በተደጋጋሚ የታየ እውነታ ነው። የኦሮሞ ህዝብ እያካሄደ ላለው ፍትሃዊ ትግል ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት፡ ***"ፀረ-ሰላም፤ ፀረ-ልማት፤ ኣሸባሪዎች"*** የሚሉና የመሳሰሉትን ስሞች በመስጠት በጅምላ መግደል፤ ማሰር፤ መደብደብና ከሃገር እንዲሰደዱ ማድረግ በኢትዮጵያ መንግስታት ሲወሰድ የነበረና እየተወሰድ ያለ እርምጃ ነው።

በኣሁኑ ወቅት የኦሮሞ ተማሪዎችና ወጣቶች እንዲሁም ህዝቡ በመላው ኦሮሚያ ውስጥ የመብት ጥያቄ በማንሳት እያካሄዱት ላለው የተቃውሞ ሰልፍ እያገኙት ያለው ምላሽ በዘግኛኝ ሁኔታ መግደል፤ መደብደብና ማሰር እየሆነ ነው።
በወያኔ ስርዓት መሪዎች ትዕዛዝ በስርዓቱ ታማኝ የጦር ሃይል በኦሮሞ ልጆችና በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየተወሰደ ባለው እርምጃ በኣምቦ፤ በመደ-ወላቡና በሌሎችም ቦታዎች እድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት የሚገኙበት በርካታ የኦሮሞ ዜጎች ተገድለዋል። በኣምቦና በሃረማያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ባዶ እጆቻቸውን በሆኑ ተማሪዎችና በህዝቡ ላይ ቦምብ በማፈንዳት ህይወታቸው ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ እየተቀጠፈ ይገኛል፤ ኣያሌ ዜጎች እስር ቤት ታጉረዋል። ሕጻናትና ኣዛውንት ትንሽና ትልቅ ሳይሉ በሁሉም በታዎች በኦሮሞ ዜጎች ላይ እየተፈጸመ ያለው ድብደባ እጅግ ዘግናኝ ነው።
ይህ እየተወሰደ ያለው እርምጃም በኣምቦ፤ ደምቢ-ዶሎ፤ ነቀምቴ፤ ጌዶ፤ ሆሮ-ጉዱሩ፥ ባሌ፤ ጭሮና ከኦሮምያም ውጪ በትግራይ መቀሌና በጎጃም ውስጥ የመብት ጥያቄ ባነሱ የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ሲወሰድ በነበረው የግድያ፤ የጅምላ እስራትና ከትምህርት ገበታ የማባረር ቀጣይ ኣካል ነው።

የወያኔ መንግስት ህዝቡ ላነሳው የመብት ጥያቄ ኣጥጋቢ ምላሽ ከመስጠት በሃይል እርምጃ ማፈን መወሰኑን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ኣጥብቆ ያወግዛል። ይህንን በልዩ የጦር ሃይል፤ ፌዴራል ፖሊስና ታጣቂዎች እየተወሰደ ያለውን ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ በማዘዝና በማስፈጸሙ ረገድ እጃቸው ያለበት፡ የስርዓቱ ጠ/ሚኒስትር፤ የወያኔ መንግስት የጦር ሃይል ኣዛዥና የደህንነት ሃላፊ ተጠያቂ መሆናቸውን ያስገነዝባል። ከዚህም በተጨማሪ በስርዓቱ የጦርና ፖሊስ ሃይሎች ውስጥ ኣባል የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች እየተገደሉ፤ እየታሰሩና እየተደበደቡ ያሉት ኣባቶቻቸውና እናቶቻቸው፤ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ባጠቃላይ ወገናቸው መሆኑን ተረድተው እየተወሰደ ባለው ኣረመኔያዊና ጠላታዊ እርምጃ እንዳይሳተፉ ብቻ ሳይሆን፡ ድርጊቱን እንዲቃወሙት አነግ በድጋሚ መልዕክቱን ያስተላልፋል።

በሃገር ቤትም ሆነ በውጪ ሃገራት ያለው የኦሮሞ ህዝብ ካሁን በኋላ ወደ ዳር ተገፍተን ኣማራጭ በመነፈጋችን የቀረው የመጨረሻው ኣማራጭ፡ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለመብቱ መታገልና ባለፉት 22 ዓመታት የተገደሉትን ልጆቹንና አሁንም ያለ ርሕራሄ በጅምላ እየተገደሉ ያሉትን ልጆቹን ደም ለማስመለስ በህጋዊው መንገድም ሆንነ በተቻለለት ሁሉ እንዲታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን። በተለይም በተለያዩ የውጪ ሃገራት የምትገኙ ዜጎች ሃገር ቤት ያለውን ህዝብ ድምጽ ለማሰማት እንድትንቀሳቀሱና ወገናዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ ጥሪ እናስተላልፍላችኋለን።

የኣለም ማህበረሰብ፤ ለሰብዓዊ መብትና ዲሞክራሲ የሚሟገቱ ድርጅቶችና ኣካላት ሁሉ፡ ኣምባገነኑ የወያኔ መንግስት የዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ጥያቄ ባነሱ ንጹሃን ዜጎች ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ ጸረ-ዲሞክራሲ መሆኑን ተገንዝበው፡ ድርጊቱን በአስቸኳይ እንዲገታ ኣስፈላጊውን ጫና እንዲያሳድሩበት እያሳሰበ፥ ይህንን ድርጊት በዝምታ መመልከት እንደተቀደሰ ተግባር ቆጥሮ ከድርጊቱ እንደመካፈል የሚታይ መሆኑን የኦሮሞ ነጻነት ግንባት በድጋሚ ማስገንዘብ ይወዳል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓም**